# ኢሣትና የሕዳሴ ግድባችን!!!

<



## ደርሶልኝ አይቼው ጀርመን! (Germany)

ይህን መጣጥፍ የጀመርኩት "ሕልም ተፈርቶ ሣይተኛ አይቀርም" በሚል ርዕስ ነበር፤ ኢህአዲግ በትረ-ስልጣን ከያዘ ወዲህ ከብዙ ወገኖችና ፓርቲዎች ስፍር-ቁጥር በሌለው መጠን የሚሰማውና የሚነበበው "የኢትዮጵያ አንድነትና ሕልውና በእጅጉ ያሰጋናል ያሳስበናል ... " የሚል ስለሆነ በዚህ ረገድ የበኩሌን የማለት ውጥን ነበረኝ። ስጋት እንደ ምክንያቱ ደረጃ ግንዛቤ ውስጥ የሚገባ እንደሆነ ቢታወቅም አሣማኝ በሆነ መንገድ ከመፍትሄ ጋር ካልተያያዘ መሰረት የሌለው ፍርሐት ወይም ቅዠትን ያስከትላል፤ ተከባብረን በአንድነት እንኑር እያልን በየቀኑ በመንሰብከው ሕዝባችን ላይ አለመረጋጋትን ያስከትላል።

ኢትዮጵያችን ዛሬም አለች፤ እንዲያውም የአካባቢው ኃያል ሀገር ሆናለች፣ ያለ ሀገራችን ብርቱ ድጋፍ በሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ሶማሌ የሚታየው መጠነኛ መረጋጋት በቀውስና ብጥብጥ መዘፈቁ አይቀሬ ብቻ ሳይሆን ጦሱ ለኛም ይተርፍ ነበር። ስለዚህም የራሳችንን ሕልውና በራችንን ሣያንኳኳ በሩቁ እየተከላከልን ነው የመንግስት ክልላዊ መዋቅር በዘርና ቋንቋ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ስጋትና ቅሬታን ከመፍትሄ ጋር ማቅረቡ አስፈላጊነት ካለው፤ ብሶትን ማጕላትና ችግሮችን ማባባስ ሌላ ችግር ይወልዳል እንጂ መፍትሄ አይሆንምና!

የዛሬ 3 ዓመት አካባቢ ኢሣት የተሰኘው የቴሌቪዥን ጣቢያ ስርጭቱን እንደጀመረ የመጀመሪያው 6 ወራት የዕወቁኝ ልመና የበዛበት ነበር፤ ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ መጀመር ጋር ግን ፅንፈኞችን እያስተባበረ በዚህ ዙሪያ በዋናነትና በሌሎችም ጉዳዮች አድማሱን እያሰፋ በመሄድ ዛሬ ሁለቱም ጐን ለጐን በራሳቸው የዕድገት መጠን ግን በተለያዩ መንገድ እንደሚጓዙ እናያለን፤ የዋልድባ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት፣ የግልገል ጊቤ ኃይል ማመንጫ፣ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት በጊዜያዊነት መነሳትን የመሳሰሉት ዓላማቻውና ግባቸው ተደብቆ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ቢውሉም፣ ይህን በማስተባበር ግንባር ቀደም የነበሩ ደካሞች አንገታቸውን ሲደፉ ሕዝቡን በማዳናገር አትራፊ ሆኖ የተገኘው ኢሣት ብቻ ነው፤ ብዙ ተመልካች አግኝቷልና! በመግቢያዬ ላይ አንደጠቀስኩት የፅሑፌን ርዐስ እንደለውጥ ያነሳሳኝ

በአሁኑ ወቅት ሁላችንም እንደምናየውና እንደምንሰማው የኢሣት ዋናው ትኩረት የሕዳሴው ግድብ እንደመሆኑ በዚህ በኩል ኢሣት የሚኖረውን ሚና እንደገና እንደያስብበት ለማስታወስና አፍራሽነቱን ለመጠቆም ነው።

ታላቁ ግድባችን የተጀመረበትን 2ኛ ዓመት በስራ ያሳለፈ ሲሆን፣ ኢሣት ደግሞ 3ኛ ዓመቱን ለማክበር ፈንዱ-ጐላ እያለ ይገኛል። ለመሆኑ ኢሣት ግድባችንን ከመገንባት ያስቀረዋል? ወይስ በተቃራኒው? አሁን እንደምንታዘበው ፅንፈኞቹን በማስተባበር አንድ እርምጃ የቀደመ ይመስላል፣ ለነገሩ ግድቡንስ በአንድ ዓመት ይቀድመው የለ? አያስደንቅም፤ የመጨረሻውን ውጤት ሩሲያን እንደሚሉት እንኖራለን፣እናያለን! ማለቱ ይሻላል።

ሰኔ 29 ቀን 2005 ዓ.ም. በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያና በሌሎችም ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ በተቃዋሚዎችና በገዥው ፓርቲ መካከል የተደረገውን የቴሌቪዥን ሙግት የተከታተለ ሁሉ ያረጋገጠው በ2ቱም ዙር ውይይት የአንድነት ፓርቲ በዜሮ መሸነፉን ነው። ከቀናት በኋላ የተገረሰሱት የግብፁ  ሙርሲ በየአደባባይና በአልጀዚራ ሳይቀር "ለአባይ ደሜን ማፍሰስ ሲያንሰኝ ነው ... ሁሉም አማራጮች ጠረጴዛዬ ላይ ናቸው...." ባሉበት ወቅት ከአንድነት የወጣላቸውን የድጋፍ መግለጫ ከራሳቸው ሕዝብ እንኳ አላገኙትም፤ በራሰጌና የግርጌ ማህተም አስደግፈው ለሁሉም ከበተኑ በኋላ እየተናነቃቸው በቃላት ለማስተካከል የሞከሩት የፓርቲው ተወካይ ሽንፈታቸውን ከማረጋገጥ ሌላ ምንም ከልፈየደላቸውም፣ እንዲያውም ይህን መሰል አጋጣሚ  በዕግር በፈረስ የሚፈልገው ኢሣት የሣምንት ቀለብ ነው የሆነለት። ሀፍረትን በመሸፈንና ስህተትን በማረም ፋንታ እንደ ትልቅ የፖለቲካ ስኬት ነው የተወሰደው በኢሣት! በ1950ዎቹ ላይ ጋማል አብዱልናስር "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ያሉትን ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በኋላ የሀገራችን ተቃዋሚዎች በተግበር ሲያውላቸው ገነትም ሆነ ገሃነም ውስጥ ይሁኑ ምን ይሰማቸው ይሆን? ለዚያውም በአባይ ጉዳይ! ያሣፍራል።

ሰኔ 12 ቀን 2005 ኢሣት ባስተላለፈው ዜና የኢህአዴግ ደጋፊዎች የደያስፖራውን ፖሊሲ ለማፅደቅ ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ የሚል ዜና በስዕል በስዕል አስደግፎ አሣይቶናል፣ የዜናው ዋና መልዕክት "ደጋፊዎች" የሚለው እንደሆነ አንባቢ እንዲረዳልኝ እፈለጋለሁ። በመሰረቱ "ደጋፊ" የሚለው ቃል በአንድ ፓርቲ መዋቅር ውስጥ ለአባልነት የተዘጋጀና የፓርተውን ፕሮግራም ተቀብሎ እንደችሎታው የሚያስፈፅም ማለት ሲሆን ከስብሰባው ተሳታፊዎች መካከል ሊኖሩ እንደሚችሉና መብታቸው እንደሆነ ብገነዘብም እኔን ጨምሮ አብዛኛው መልዕክተኛ የሕዳሴው ግድብ እንጂ የኢህአዴግ ደጋፊ አልነበረም፤ የዚህ መሰሪ ዜና ግብ ለሕዳሴው ግድብ ሙሉ እምነት ያላቸውን ዜጐች ለማሸማቀቅና ለማሳጣት ሆን ተብሎ የተላለፈ ነው።

በአውሮፓ የኢህአፓ አባላት እምብዛም አይታወቁም ሰላማዊ ሰልፍንም ሆነ ሌላውን ደርበው የሚሰሩት ደጋፊዎች ናቸው ታዲያ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ የቀረፃቸው ወገኖች በለበሱት ካኒቴራ "NILE" የሚለው ፅሑፍ ሣይታየው ቀርቶ ሣይሆን የኢሣት ፍላጐት የግድቡን ስራ ማኮላሸትና ከተቻለም ለሕዳሴው የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ወደራሱ የሚዛወርበትን መንገድ ማመቻቸት ነው፤ የራሱ ቶምቦላ ማስተወቂያ እንደሚለው "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ!!" በተለያዩ አገራት በራሳቸው ፍላጐት የተዋቀሩ

የግድቡ ድጋፍ አስተባባሪ ም/ቤቶች ተግባራቸውን፤ የሚያከናውኑት ለሀገራችን ሁለገብ ዕድገት ዕገዛ እንደሚያደርግና በተለይም ሉዓላዊነታችንን ያረጋግጣል ከሚል ፅኑ ዕምነት በመነሳት እንጂ አስፈላጊውን ዕገዛ ከማድረግ ባለፈ የትኛውም ኤምባሲ ጣልቃ የሚገባበትና ጫና የሚያደርግበት አይደለም የኢሣት ደጋፊዎች በየቦታው አንደሚያደርጉት ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ለእነርሱ ያላጨበጨበ ሁሉ ወዲያውኑ በጠላትነት ስለሚፈረጅ የአባላቱን ስም በማጥፋት፣ በማስፈራራትና ከዚህም ባለፈ ደረጃ ከሕብረተ-ሰቡ ለማግለል የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡

ኢሣት ዳፉ ቀና አያላ የሚገኘው ከሰብዓዊ መብትና መስተካከል ከሚገባቸው የመንግስት ፖሊሲዎች አኳያ ሣይሆን ዲያስፖራውን ለሁለት ከፍሎ እያቆራቆሰ የራሱን ገቢ ለማዳበር እንደሆነ በግልፅ የሚታይ ዕውነታ ነው፡፡ ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ እራሱ በሚያደርገው ዝግጅት ላይ ከሌላው ወገን እስከአሁን የተቃወመው የለም፣ ምክንያቱም የሌሎችን መብት እስካልተጋፉ ድረስ ሁሉም የራሱን አመለካከት የማራመድ ሙሉ ነፃነት እንዳለው ዕምነታችን ስለሆነ ነው፡፡ ይህን እንደ ፍርሐት ቆጥሮት ከሆነ ለወደፊቱ በየከተማው የሰገሰጋቸው ፅንፈኞችና ጀሌዎች ይህን መሰል ዕድል እንደማያገኙ ከወዲሁ ሊገነዘበው ይገባል፡፡ እነሱ ዓየር ላይ ለመበተን በየሀገሩና በየመንደሩ የሚሰበስቡት ገንዘብ ሕጋዊ ሲሆን ሀገር ወዳዱ ዜጋ ካለው ቀንሶ የሚሰጠውን ድጋፍ ደግሞ ሕገ-ወጥ ያደርገዋል፤ ዓላማው ግልፅና የማያሻማ ነው፤ "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ!! አንድም ገቢውን በሙሉ ማግኘት አለበት አለያም ያለሱ ፈቃድ ምንም መደረግ የለበትም ይህንንም ተቃዋዊ ወገን በሚሉ መሣሪያዎቹ አማካይነት ለዓለም ባንክ አውሮፓ ሕብረትና ለሌሎችም በሰልፍ ብቻ ሣይሆን በፅሑፍ ሣይቀር ተማፅኗል፡፡

የትኛውም የኤኮኖሚ ማዕቀብ በቀጥታ የሚጐዳው ሕዝቡን እንጂ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በዚህ ዘዴ እንደማይንበረከክ የኩባ፣ ሰሜን፣ ኮሪያ፣ ኢራን፣ ከኢራቅና የሌሎች ሀገሮች ምሣሌ በቂ ማስረጃ ነው፤ አንድን መንግስት ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፎካከር፣ መቃዎምና ከዚያም አልፎ እንደሆኔታው ተጨማሪ ፓለቲካዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንጂ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሕዝቡን የሚጐዳ ተግባር መፈፀም ይቅር የማይባል ወንጀል ነው፤ ዕውነትም ይሁን ወይም የተጋነነ የሮበርት ሙጋቤ ባለቤት ሆንግ ኮንግ ድረስ ለገቢያ እንደሄደችና ውድ ዕቃዎችን እንደሸመተች ሰምተናል፤ በወርቅና ድንቅ በሆነው የአልማዝ ማዕድን የምትታወቀው ዚምባቡዌ ዛሬ ኤኮኖሚዋ በማዕቀቡ ምክንያት ተንኮታኩቷል፤ ባጭር ምሣሌ ለመግለፅ አንድ ቢሊዮን የዙምባቡዌ ዶላር የኛን አንድ ብር ያህል ዋጋ የለውም፡፡ ሆኖም ከዚምባቡዌ አንድ ነገር መማር ይቻላል፤ ይቅር፣ መባባልን፣ ከስልጣን ሽሚያ ይልቅ የሀገር ጥቅም ማስቀደምን፤ የተቃዋሚው ፓርቲ መሪ ባለፈው ምርጫ ወቅት መሸነፍ ብቻ ሣይሆን የዱላ ውርጅብኝና ዕስራትም ደርሶባቸዋል፤ ሆኖም የሀገሪቱን ሰላምና የሕዝቡን አንድነት ለመጠበቅ ሲሉ ከመንግስት ጋር ተቀራርበው አብሮ እስከመሰራት ደርሰዋል፡፡ በአሁኑ ምርጫ እንደተሸነፉ ቢያውቁም በድምጽ አሰጣጥ ላይ ያደረባቸውን ቅሬታ ለሕገ-መንግስታዊ ፍርድ ቤት አቀረቡ እንጂ ዓመፅ አላካሄዱም፣ የኛ ፖለቲከኞች ግን የአዲስ አበባ ከንቲባነት ብቻ ሣይሆን የቤት-መንግስት ቁልፍ አብሮ ካልተሰጠን ብለው በፈጠሩት አምቢተኝነት በቁጥር ቀላል የማይባል ወገኖችን ለሞትና ዕስራት ተደረገ፣ ጭዋነት የጐደለውን ዓፀፉ በመፍራት ዛሬም አፉን ሞልቶ የሚናገራቸው የለም፡፡

አሁን እንደምናዬው የፖለቲካ ተመክሮና የሰከነ አመለካከት ያላቸው ወገኖች ድምፅ እየታፈነ የፅንፈኞችና ጀብደኞች ታምቡርና ቱማታ ነው። የዳያስፖራን ጐራ የሞላው፣ አቶ ስዬ አብረሃና ወ/ት ብርቱኳን ሚደቅሳ ለዓመታት መታሰራቸው እያታወቀ ከይቅር ባይነትና ሰብዓዊነት በመነጨ ስሜት በመለስ ሕልፈተ-ሕይወት ኃዘናቸውን ስለገለፁ ብቻ የመርገም ጨርቅ ተደርገዋል፤ ፅናቱንና ብርታቱን ይስጠውና ወንድሜ እስክንድር ነጋ አገኘ የተባለውን የምንትስ ቅብንጥርስ "ሽልማት" እነ ዳዊት ከበደም አላቸው፤ አስራትም ደርሶባቸዋል፤ የመካከለኛው ምስራቅና የሁሉም ፖለቲካ ሊቀ-ሊቃውንት ሲሉት የነበረው አቶ ጃዋር ደግሞ የግል አስተያየት በመስጠቱ ብቻ ከሰማይ አውርደውታል። ወጣቱ ምሑር የገለፀው እምነቱንና የማንነቱን መሰረት እንጂ ኢትዮጵያዊነቱን እልካደም፤ ሌላው ቀርቶ ሌላም ለሌሎቻችን የማይመች ቢናገር እንኳ አመክኒዮ ባለውና ገንቢ በሆነ መልኩ የሚባለውን ማለት ሲገባ "ቤተ-መቅደስ የገባች ...." ማድረግ ፍፁም ተቀባይነት የለውም። በእኛ አንደበት ካልተናገርክ እንደ እኛ ጭንቅላት ካላሰብክ ዋጋህ ታገኛለህ ነው የጋጠወጦች መፈክር። ብሔራዊ መግባባት እንዳይፈጠር መሰናክሎች ኢሣትና ከሱ ጐን ወይም በስተጀርባ ያሉ ክፍሎች ለመሆናቸው ያፈጠጠና ያገጠጠ ዕውነታ ነው፣ ለሙያው ነፃነትና ለታሰሩ ጓደኞቹ መፈታት ጋዜጠኛ አበበ ገላው በሬጋን ቤት ያለውን እንደሰማን በሱ እምነት ሕዝቡ የፈለገውን ያህል ይራብ የሚበቃውን ያህል እስካወራ ድረስ ትክክለኛው ዲሞክራሲ ያ ነው። ሰላምና ዲሞክራሲን እኔም እደግፋለሁ፣ ሁሉም ይደሰታል ይመኛል ግን ከሁሉ በፊት ሕዝባችን ዳቦ ማግኘት አለበት፣ ዲሞክራሲ በዓዋጅ የሚሰጥ ሣይሆን ከሕብረተሰቡ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ጋር አብሮ የሚዳብር ስለሆነ ጐን ለጐን አብረው እንዲጓዙ ማድረግ ይቻላል።

ሰሞኑን አዲስ አበባ ውስጥ ከመንግስት በሚሰጥ ቅድሚያ ብድርና ድጋፍ 40/60 የተሰኘ መኖሪያና ሌላም ዓይነት ቤት ይሰራል፤ የሚል ዜና ከመሰራጨቱ ምድረ-ዳያስፖራ ሁሉንም የኤምባሲ ጽ/ቤት አጨናንቆታል፤ ቤትም ሆነ ሌላ ሀብትና ንብረት ማፍራት የሁሉም ዜጋ መብት እንደሆነ ጥያቄ ውስጥ ባይገባም ከእያንዳንዱ መብት ጐን ደግሞ ግዴታ መኖሩ ሊዘነጋ አይገባውም፤ አብዛኛው ዜጋ ሲመለስ የሚገባበት ጐጆ ለመቀለስ የተፈጠረለት አጋጣሚ ቢያስደስተውም ኢሣትንና በየቦታው የመደባቸውን አክራሪዎች ከመፍራቱ የተነሣ ሁሉም በድብቅ እንዲሆንለት ይፈልጋል። እነኝህ ወገኖች ከተሳካላቸው ኢሣት "ወያኔ" እንደሚላቸው ሣይታለም የተፈታ ነው ይለቁንም ፅንፈኞችና አክራሪዎች ባንድ በኩል ሀገራዊ ተግባርን እያደናቀፉ በሌላ ወገን ደግሞ ሞራል የሌላቸው ስለሆኑ እንደ ሚሌኒየሙ ጊዜ ሁሉ በዚህም በዚያም ለማምታታት ይጠቅማናል ያሉትን የጓሮ በር ከማንኳኳት አይመለሱም፤ በመሆኑም "... የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" ዓይነት እንዳይሆን መንግስት ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግ ዘንድ ግድ ይላል።

ኢሣት ሚዛን የጐደለው የዜና ማሰራጫ ነው፤ ወይም ሕዝቡን ትርምስ ውስጥ በማስገባት ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚቋምጥ አካል ልሳን ነው። የሁሉንም አመለካከት ለማስተናገድ ፍላጐት ቢኖረው ከአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያና ከዶቼ ቬሌ መማር ይችል ነበር። ተፈጥሮው ስለማይፈቅድለትና ዓይንና ጆሮነቱ ለራሱ ጥቅም ብቻ ስለሆነ በየቦታው ላስቀመጣቸው ክሊኮቹ ስልክ እየደወለ ሀገር እንደፈረሰ፣ ሕዝብ እንተደጨረሰ ከማላዘን ለላ እስከዛሬ አንድም ለሀገራችን የሚጠቅምና መፍትሄ አዘል የሆነ ፕሮግራም አላቀረበም። በመሆኑም "እኔን ጐዳሁ ብላ...." እንደሚባለው መንግስትን ያጠቃ መስሎት

ያለምንም ሀፍረት ከጠላት ጋር መቆሙን በገሃድ አረጋግጧል። እንዲያውም በግብፅ የሚደገፉ ተቃዋሚዎች ሶማሌ እንደገቡ ነው በኩራት የገለፀልን።

በዓለም ዙሪያ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው 2 ሚሊዮን ዳያስፖራ መካከል የኢሣት ደጋፊና "ተቃዋሚ" የተሰኘው አክራሪ ክፍል ከ5000 አየበልጥም፤ ምግባረ-ብልሹነቱንና ለከት የሌለውን የስድብ ውርጅብኝ በመፍራት በየቤቱ የተቀመጠው ብዙሃኑ ወገናችን ግን ፅኑዕ በሆነ የሀገር ፍቅር ስሜት የታነፀ ነው። ኢሣት እራሱን ከፈጠረው አካል ሌላ የሌሎችን ሕልውናና ዕድገት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አጥብቆ ይቃወማል፤ ለምሣሌ የሰማያዊ ፓርቲ አጀማመር "ይበል!" የሚያሰኝ ነበር፣ ነገር ግን ሰላማዊ ሰልፉ ሲደረግ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ለጋራ ዓላማና ብሔራዊ ጉዳይ እንጂ የሰልፉ መድረክና አደባባይ "ሶላት" የሚደረግበት መስጊድ ወይም "የሚቀደስበት" ቤተክርስቲያን ሊሆን አይገባውም "የቄሳርን ለቄሳር...." እንደሚባለው እምነት ለአማኞችና በራሳቸው መፍትሄ ማግኘት አለበት እንጂ ከፖለቲካ ጋር መቀየጥ የለበትም፤ ባንድ ኃይማኖት ጥላ ስር ከሚገኘው የአረቡ ዓለም ውጭ በየትኛውም የዓለም ክፍል የለም፤ አሜሪካም፣ አውሮፓም! ኢሣት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገና ማቆጥቆጥ ሲጀምሩ ወደ ስህተት እያመራና ያልሆነ ሞራል እየሰጠ ያሳብጣቸውና ቶሎ እንዲፈነዱ ያደርጋቸዋል፤ ስለዚህም የአንድነት ፓርቲ ከግብፅ ጋር መወገንና የሰማያዊ ፓርቲ እምነትን እና ፖለቲካን አለመለየት ብዙሃኑ-ፓርቲ ያለበት ሕብረተሰብ እንደሚመኝ ማንኛውም ዜጋ ያሳስበኛል፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንዳየነው እስላሞች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ቅሬታቸውን የገለፁትና አቤቱታ ያሰሙት በፍጹም ጨዋነት ነው፣ ይህ ትዕግስትና መልካም ዓርዓያነት የመነግስትን አቅል መሣቡ አያጠራጥርም።

የኮሚኒዝምን መውደቅ ተከትሎ በሶሻሊዝም ስም በሕዝቡ ላይ ለደረሰው በደል ይፋ ይቅርታ የጠየቀው የቼክ ሪፑብሊክ ኮሙኒስት ፓርቲ፣ ፓርላማና መንግስት እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቧል፤ ሌላው የፈፀመውን ሰህተትም ሆነ ያደረሰውን በደል በሂደት ያስተካክላል ወይም ይወርዳል፤ ሁሉንም እንደ ሰራው የሚዳኘው፤ ሕዝብና ታሪክ ብቻ ነው። ኢህአዴግ ስልጣን እንዳያዘ ብዙ ስህተቶች መፈፀሙን አምናለሁ። ሆኖም የሀገሪቱን አንድነት ከመጠበቅ አንፃር ሌሎች ስህተቶችን በመለስተኛ ደረጃ ነው የማያቸው ወቅቱ ምስራቅ አውሮፓ ፍርክስክሱ የወጣበት ጊዜ እንደመሆኑ ባንዴ ከ25 በላይ አዳዲስ አገሮች እንደተፈጠሩ እናስታውቃለን። መገንጠልና ማስገንጠል ቢፈልግ ከዚያ የተሻለ ሁኔታ እንዳለነበረ ለሁላችንም ግልፅ ነው። የጊዜው ፋሽን ነበር ማለት ይቻላልና! ነፃነት የፈለገ ሕዝብ የሞተለትንና የታገለለትን በጥቅማ-ጥቅም ይለውጣል ማለት ዘበት ነው፤ ሻዕበያ ከኢትዮጵያ ጋር መኖር ቢፈለግ የኤኮኖሚና የአመራር ድርሻውን የሚነፍገው አልነበረም፤ እሱ ግን "ያልተሸረፈና ያልተቀነሰ" ነፃነቱን ነው የመረጠው. አግኝቷልም። በመሆኑም ህዋሃት ለኤኮኖሚ ጥቅም ሲል ብቻ ነው በኢትዮጵያ ጥላ ስር የቆየው! የሚለው ብሒል ወንዝ የሚያሻግር አይደለም፤ አይሆንምም፤ ከዚህም በመነሳት በአንዳንድ አፅንኦቶች ለማስደገፍ የኢህአዴግ መንግስት፡-

1. ሕገ-መንግስቱ ላይ በውል የሰፈረ ጠንካራ ፌዴሬሽን መስርቷል፤ የመገንጠል መብት እንዳለ ይገለፅ እንጂ አንቀጽ 39 ቁጥር 4 ላይ ከ"ሀ" እስከ "ሠ" የሰፈረውን ለሚገነዘብ በዘፈቀደ የሚሆን ሣይሆን የጠበቀና በቀላሉ የሚይበጠስ ነው።

2. ሰንደቅ ዓላማችንን በተመለከተ የሚገባውን ክብር እስካልሰጠነው ድረስ በየትኛውም ስፍራ አናውለብልበው ወይም ተሸክመነው አንዙር ብሐራዊ ኩራትን ስለማይገልፅ፤ ዛሬ ሁሉም ተስተካክሎ በየትምህርት ቤቱና በሌሎችም ተገቢ ቦታዎች በሰርዓት ተስቀሎ እንዲወርር ድና የራሱ የሆነ ቀን ጭምር እንዲኖረው ተደርጓል፡፡
3. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ አፍሪካ ሕብረት) ከሀገራችን ተነስቶ ነበር ማለት ይቻላል፣ በተለመደው የፈጣሪ ዕገዛና ባንድ ሰው ትግል ነው የቀረው፣ ቶጐ-ሎሜ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ ከ53 መሪዎች ጋር ብቻቸውን ያደረጉት ተጋድሎ ዓፄ ኃ/ሥላሴ ጄኔቭ ላይ ካሰሙት አቤቱታ ይልቃል እንጂ አያንስም፤ በጋዳፊ ገንዘብና በግብፅ መሰሪ ፓለቲካ የተገዙ የክፈለ ዓለማችን ሆዳም መሪዎች ሀገራችን ለነፃነታቸው ያደረገችላቸውን ሁለ-ገብ ድጋፍ ዘንግተው ሕሊናቻውን በገንዘብ ቢለውጡም አቶ መለስ "ዛሬ፣ አሁኑኑ ወሳኔ ስጡኝ" በማለት ወደር በሌለው የሀገር ፍቅር ስሜት ቤቱን ገትረው በመያዛቸው ነው ያሸነፉት፤ ለጥቅም ብቻ የቆመና ሀገሩ እንድትበተን የሚፈለግ አመራር እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ የበለጠ ይረዳዋል እንጂ በተቃራኒው አምርሮ የሚታገልበት ምክንያት የለም፡፡ ለዚህ ነው የምንከሰውንና የምንወቅሰውን ያህል ለመንግስት በጐ ስራና ማስተካከያ ያልተጋነነ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል የምለው፡፡
4. የፌዴሬሽን መዋቅር እንኳን የተለያዩ ሕብረተ ሰብ የማገኙበት ኢትዮጵያችን ይቅርና በአንድ ብሐርም ይዘረጋል፤ የጀርመን ሕዝብ የዘር-ግንዱ ቋንቋውና ባህሉ አንድ ቢሆንም ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የወደቀበትን ኤኮኖሚ መልሶ ለመግንባት እንደ ብቸኛ አማራጭ የወሰደው ፌዴሬሽንን እንደሆነ ይታወቃል፤ በዚህም ዕድገቱ በፍጥነት ከመምጠቁ የተነሣ ዛሬ መላው አውሮፓ ያለ ጀርመን ትርጉም አልባ ይሆናል፤ እርግጥ ያገራችን አወቃቀር ዘርና ቋንቋን መሠረት ያደረገ መሆኑ ሰጋት መፍጠሩ አልቀረም፤ ነገር ግን በ1997ቱ ምርጫ ተቃዋሚዎች ከመነግስት ጋር ተስማምተው ቢሰሩና ቢቀራረቡ ብሐራዊ መግባባት ሊፈጠርና "ጐደለ!" የተባለው እስከዛሬ ይሟላ ነበር፣ ሌላው ቀርቶ ሕገ-መንግስቱ ሣይቀር እንዳስፈላጊነቱ የማይሻሻልበት ምክንያት አልነበረም፡፡
5. የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ድርድርና የታላቁ ሕዳሴ ግድብ አርስበርስ የተቆራኙ ናቸው፤ ከ1993ቱ የኢትዮ-ግብፅ ስምምነት በኋላ ከአባባቢው ሀገሮች ጋር ለዓመታት የዘለቀ የዲፕሎማሲ ትግል ተካሂዷል፣ ድሉ ወደኛ አያዘነበለ ሲሄድ በጐን የግድቡ ፕሮጀክት በባለሙያዎች እንዲዘጋጅ ተደረገ አብዛኛው የተፋሰስ አገሮች ስምምነቱን ከፈረሙ በኋላ ደግሞ ግንባታው ተጀመረ፣ የግድቡ ሃሣብና እቅድ ከፖለቲካ ፍጆታ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ወይም በድንገት የተወጠነ ሣይሆን ከፍተኛ ጥናት የተደረገበትና ከአረቡ አብዮት በፊት የተጠናቀቀ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ በሕብረተሰቡ ድጋፍ እንዲገነባ የተወሰነበት ምክንያት ደግሞ የግብፅ አቋም ቀደም ሲል የሚታወቅና 13 ዓመት ሙሉ በፈጀው የዲፕሎማሲ ውጣ ውረድ አንዲት እርምጃ ሣይቀር ወደ ጋራ ጥቅም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኗ የሷን "ይሁንታ" ለማግኘት ሌላ ምዕተ-ዓመትና ሚሊኒየም ላለመጠበቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ በካምፕ ዴቪድ ስምምነት የተነሣ ከአሜሪካ የሚደረግላት ድጋፍ የመካላከያ ኃይሉን በጀት በመሸፈን ብቻ ሣይወሰን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በተለይም ግብፃውያን በተለያዩ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች የገንዘብ ተቋማት በኃላፊነት ቦታ ስለሚገኙ በዚህ በኩል ብድርም ሆነ አርዳታ የማግኘት እድላችን እናሳ ስለሆነ ነው፤ ይህም ሆኖ ሕዝቡ በፋይናንስ እንዲሳተፍ

የተፈለገው የባለቤትነት ስሜቱ እንዲዳብርና የቁጠባ ባህሉ እንዲጐለብት ታስቦ የሕዝቡ ድርሻ ከአጠቃላይ ወጪው ከ14-19% ወይም ከ4-6 ሚሊዮን በላይ አይደለም፤ ከ80 በላይ የሆነውን የግንባታ ድርሻ የወሰደው እራሱ መንግስት ነው፣ ሀቁ ይህ ሆኖ ሣለ ሕዝቡ አላዋጣ አለ፣ ተገደደ ግንባታው ሊቆም ነው ... የሚለውን የኢሣት መሰረተ-ቢስ ልፈፋ ሁላችንንም ያድርሰንና ከ5 ዓመት በኋላ እናየዋለን፤ የአባይ ጉዳይ የመንግስት ብቻ አይደለም፤ በአባይ አይቀለድም።

6. በውጭ ግንኙነት በኩል ባለፉት 20 ዓመታት እንደ ኢትዮጵያ የተሳካላት ሌላ አገር የለም፤ ብሎ ደፍሮ መናገር ይቻላል፤ በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ ፊቷን ወደ ቻይና ባዞረች ጊዜ "ወዳጃችንና እረዳታችን የሆነችውን አሜሪካን ያስቀይማል" የሚል ወቀሳ ከየአቅጣጫው በመንግስት ላይ ይሰማ እንደነበር እናስታውሳለን፤ ዛሬ ላይ ቆመን ስናዬው የአመራሩን ትክክለኛነት ብቻ ሣይሆን አርቆ አስተዋይነቱንና ብልህነቱን የሚያረጋግጥ ከመሆኑም ሌላ የተለያዩ ሥርዓት ከሚከተሉ ኃያላን ሀገራት ጋር ሚዛን በመጠበቅ ሁሉም የሚፈልገውን እንደ አቅምና ደረጃ እየሰጡ በዓፀፋው ለዕድገታችንና ልማታችን እንዲሁም ለዳህነታችን የሚያስፈልገውን በማግኘት ረገድ የተሳካና የማያኮራ ተግባር ተከናውኗል፤ በዚያ ወቀት የበኩር ልጅ ለመሆን የቋመጠው የኤርትራ አገዛዝ የቃየልን ቦታ በመውሰድ የተረገመ ትውልድ ድርሻውን ይዞ ከአሸባሪዎች ጉያ በመሸጐጥ አረጋግጧል። ይህም ተጨማሪ ጡጫና እርግጫ ያስከትላል እንጂ ከወደቀበት የሚያነሣው አይሆንም።

ከዚህ በላይ በመጠኑም ቢሆን የመንግስትን በጐ ጐኖች አውስቻላሁ፤ በውዳሴና ምስጋና ብቻ መወሰን ልማዴ ስላልሆነ መታረምና መስተካከል ይገባቸዋል፤ የምላቸውን ደግሞ ባጭሩ እንደሚከተለው ዕጠቁማለሁ።

1. የሕዝብ መፈናቀል፡- ሕገ-መንግስቱ ሕዝቦች በሀገራችን ሁሉም ቦታ የመኖር፣ የመዘዋወርና ኃብት የማፍራት መብት አጐናፀፋቸዋል፤ ይህ ብሔራዊ ብቻ ሣይሆን ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት እንደቀላል ነገር በተወሰኑ ሙሰኞች ሲደረመስ በደረቅ ወንጀል ብቻ መታየት ያለበትም፤ የአማራን ክልላዊ መስተዳድር ቦታው ድረስ በመሄድ ጠይቄ እንደተረዳሁት ከቤንሻጉል ተፈናቅለው እንዲመለሱ የተደረጉ ወገኖች ሁኔታው በድጋሚ እንዳይፈጠር ከክልሉ የተላኩ ባለሙያዎች ተመድበውላቸው ደህንንታቸውነና ጥቅማቸውን እያስጠበቁላቸው እንደሆነ ተነግሮኛል፤ ሆኖም፣ በጥበቃና በስጋት የሚኖር ሙሉ ነፃነት ስለማይሰማው ይህን መሰል ሁኔታ እንደገና ቢከሰት ግልገል ባለሥልጣኖች ብቻ ሣይሆኑ የበላይ ኃላፊዎች ጭምር በቀጥታ የሚጠየቁበት መንገድ ተጠንቶና ተዘጋጅቶ ዘላቂ መፍትሄ ሊገኝለት ይገባል፤ ከዚያ በፊት ግን በየትኛውም የሀገራችን ክልል የተፈናቀሉ ዜጐቻችን የተወሰደባቸውን ወይም የተቀሙትን ንብረት ማግኘት ብቻ ሣይሆን ለደረሰባቸው እንግልትና በደል ተመጣጣኝ ካሣ ሊከፈላቸው ያስፈልጋል፤ ወጭውን በመሸፈን በኩል ከመንግስት በተጨማሪ ወንጀሉን የፈፀሙ ግለሰቦችና ክልሉ የድርሻቸውን መከፈል አለባቸው፤ ይህ ሲሆን ብቻ ነው የመንግስት ተዓማኒነት የሚጨምረውና ሌሎችም ከተመሣሣይ አድራጐት መቆጠብ የሚችሉት፣

2. የሙስሊሞችን ጥያቄ አስመልክቶ የዕምነቱ ዕውቀት ባይኖረኝም ከፊሉም ሆነ አብዛኛው ቅሬታ እስካለው ድረስ አስቸኳይና ፍትሃዊ መልስ ያሻዋል፤ ምሽጋቸውን አውሮፓና አሜሪካ ያደረጉ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች እነሱ የሌላቸውን ወኔና የሚፈልጉትን ስልጣን ለማግኘት ቀቢፀ-ተስፋ ያደረጉት ሕዝቡን በኃይማኖትና በዘር እየለዩ በማቆራቆስ የሚገኘውን ውጠት ነው፤ ለዚህም ከግብፅ ሣየቀር ፅንፈኛ ሰባኪ በመጋበዝ በየመድረኩ ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉን ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአክራሪዎች ስብከትና ግፊት በግብፅ ስንት ቤ/ክርስቲያን እንደተቃጠለና ምን ያህል ምዕመን እንደሞተ ጉዳያቸው አይደለም፡፡ ወይም የምናውቅ አይመስላቸውም ግብፃዊው ፅንፈኛ ባንድ በኩል ሽብር እየነዛ ተጨማሪ ተልዕኮው ደግሞ ሕዝባችን በሕዳሴው ግድብ ላይ እንዳያተኩር ሳንካ መፍጠር ማዘናጋት ሲሆን የኢሣትን መፈክር ነው በጋራ የሚጠቀሙት ማለት ይቻላል፡፡ ባንድ "ድንጋይ ሁለት ወፍ!" ስለሆነም የሀገራችን ሙስሊሞች በውስጣቸው የሚታየው ልዩነት ሰላማዊ ፍፃሜ እንዲኖረው ማድረግ የመንግስት ኃላፊነት ስለሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሣይባክን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን እልባት እንዲያገኝ ማድረግ የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

3. ሙስና የስዓርዓተ- መንግስትና የሕብረተ-ሰቡ የጋራ ዕድገት ነቀርሣ ነው፤ ትክክለኛውን ትርጉም ማስቀመጥ ቢቻልም በራሴ ግንዛቤ መግለፁን መርጫለሁ፤ መንግስት በዚህ ፀረ-ሕዝብ የእድገት ደንቀራ ላይ "ዘምቼበታለሁ" ቢልም እስከአሁን ምንም ፈቀቅ አላለም፤ ኢትዮጵያ በነበርኩ ጊዜ እንደታዘብኩት ሙሰኞች በሕገ-ወጥ ተግባራቸው ሊደነግጡ ቀርቶ እንዲያውም እንደ ሕጋዊ ግብር በመውሰድ በሕዝቡ ላይ የሚወሰንበት ክፍያ እንደ ገቢውና ጉዳዩ በደረጃ የተለዩ ነው፡፡ በተለይ ከውጭ የሄደ ከሆነ ምንም ምርጫ የለውም፣ እራሱ በአካል ሲሄድ "ተወካይህ ያስጨርሰው" ይባላል፤ ተወካይ ሲሄድ ደግሞ "ባለቤቱ ይምጣ" ነው መልሱ፣ ዓይነትና መጠኑ ይለያይ እንጂ የቢሮክራሲው ግፍ ያልደረሰበት ይኖራል ብዬ አላምንም፣ በመሆኑም እኔና መሰሎቼ የደረሰብንን ትቼ በአንዲት ዜጋ የተፈፀመውን በደል አንደምሣሌ በማውሳት ልቋጨው በዕድሜ የገፉት ባልቴት ከመጀመሪያዎቹ የኮንደሚኒዬም ተመዘጋቢዎች ውስጥ ናቸው ታዲያ እክሌ ደረሰው፣ ደረሳት ... እየተባለ በጐረቤት ሲወራ ይሰሙና የሚመለከተውን ክፍለ ሲጠይቁ እርስዎማ ደርሶዎታል! ይባሉና አድራሻው ይነገራቸዋል፤ ልባቸው በደስታ እየዘለለ ታክሲ በመከራዬት ከተባለው ቦታ ሲደርሱ እንዲት ደም-ግባቷ የሚሰብ ቆንጆ ወጣት በር ላይ ትቆምና "ይህማ ለኔ ተሰጠኝኮ" ትላቸዋለች፤ እንዴተ ሊሆን ይችላል? በሚል ወደ ላካቸው አካል ተመልሰው ሲጠይቁ "የዕጣውን ውጤት በቴሌቪዥንና በጋዜጣ አሳውቀን በጊዜው ስላልቀረቡ ነው፡፡ ለሌላ የተሰጠው" ይባላሉ፤ እርሳቸውም "የግል ችሬ እሱ አይደል?" ቤት ስለሌለኝ እኮ ነው ያመለከትኩት፤ የምኖረው ሽፋን ከሌለው መፀዳጃ ቤት ጐን ፀሐይም ሆነ ዝናብ በማይከላከል ዛኒጋባ ነው፤ እያሉ ሲንሰቀሰቁ ሌሎች ባለጉዳዮች ደጋግፈው ከግቢ አስወጥተዋቸዋል፤ ደካማዋ ግለሰብ ከዚያም በኋላ ያገኙት ፍትሕም ሆነ ተለዋጭ ውሳኔ ወይንም ማስተካከያ የለም፤ በሕይወት መኖራቸውን የሚያውቀው አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከዚያ ቢሮ ሲወጡ አገራችንን እና ሕዝባችንን አምርረው መርገማቸው አይቀርም ስለሆነም መንግስት የሕዝቡን እንባ የሚጠብቅበት ተቋም ማዋቀር ብቻ ሣይሆን እርምጃ መወሰዱን እና ቢያንስ ሕዝቡ አንፃራዊ ፍትህ ማግኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ አለበለዚያ በግማሽ ልባቸው ወይም ለሆዳቸው ብለው የኢህአዲግ ደብተር የያዙ ስግብግቦች የሚበቃቸውን ያህል ካጋበሱ በኋላ

ከአገር ይወጡና እራሳቸውን እንደተበደሉ አድርገው ከኢሣት እቅፍ ውስጥ ይገባሉ። በዚህ በኩል የባሕር ዳሩ ጉባዔ ጥሩ ነው እላለሁ፤ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር በጥብቅ መቆራኘት ይኖርበታል።

ጁሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት ኤኮኖሚያችንን በተመለከተ አንዲት ነገር ልጨምር ንጉሱ ከስልጣን ሲወርዱ ደርግ የተረከበው ባዶ ካዝና እንደነበር ተነግሮናል፤ ኢህአዲክ ሲገባ ግን ካዝናው እንኳን አልነበረም፣ የአገራችን ኢኮኖሚ የሞተና ያበቃለት ነበር። በግርድፉ እንደማስታውሰው 1978/79 አካባቢ ለትግራይ ክልል የተመደበው በጀት ከሁለት መቶ ሚልዮን ብር አይበልጥም። ዛሬ እያንዳንዱ ክልል በቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ከመሆኑም በላይ የአገሪቷ ዓመታዊ በጀት ከ150 ቢልዮን ብር በላይ እንደሆነ ይገመታል። ለውጭ ገበያ የምናቀርበው የተፈጥሮ ሀብት እና የኢንዱስትሪ ውጤት ከቁጥር የሚገባ ባይሆንም፣ ተከታታይ የሆነ ዓመታዊ እድገታችንን ቅን ሕሊና ያለው ሰብአዊ ፍጡር የሚያስተባበለው አይደለም። ሆኖም መነሻችን ከዜሮ በታች ስለነበር፣ በሕዝባችን ኑሮ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማድረግ አልተቻለም። የአገራችን ኢኮኖሚ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ (GDP) 20 ቢልየን ዶላር ቢሆን እና 10% ዓመታዊ እድገት ቢገኝ ትርፉ 2 ቢልዮን ዶላር ነው። ይህ ለ80 ሚልዮን ዜጐች ቢከፋፈል በነፍስ ወከፍ 25 ዶላር ወይም 450 ብር የሚደርሰው ሲሆን፣ ላለፉት 9 ዓመታት በትክክል የሆነ ነው። በዚህም ከ20 ዓመት በፊት የሕዝቡ ዓመታዊ ገቢ ከ100 ዶላር በታች የነበረው ዛሬ ከ400 ዶላር በላይ እንደሆነ ለማረጋገጥ የኢሣትን አዎንታ ማረጋገጥ አያስፈልግም፤ በሃብት ክፍፍልና በቢሮክራሲው ማነቆነት ላይ ብዙ ማለት እና መወያየት ይቻላል፤

ከኢኮኖሚ ጠቀሜታው አንፃር ሲታይ የታላቁ ሕዳሴው ግድብ የሚኖረው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። በግሌ ከዚህ ትልቅ እንድምታ ጐን እንደዋና አድርጌ የምወስደው ግን ለአገራችን ሉአላዊነት የሚኖረው ቁልፍ ድርሻ ነው፤ ኢሣትም ይህ ፕሮጀክት ካለቀ በብዙ መልኩ ኪሣራ፤ እንደሚያደርስበት ስላወቀ ነው ያለ የሌለ ኃይሉን በዚህ ብሔራዊ አለኝታችንና ተስፋችን ላይ ያነባፀረው፤ ስለዚህ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድ ሁሉ እነዚህ እልከኞችና ግትር ወገኖች እንዲሁም ቂመኛ እና የአንድ ወገን ጋዜጠኞች ሸፍጥና ሴራ እንደነሱ አጉራ ዘለል በመሆን ሣይሆን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ባልተለየው ሁኔታ ልንታገላቸው ይገባል።

# *በአባይ ቀልድ የለም!!!*

*amizanu@yahoo.de*